የሰ/መ/ቁ. 35946

ጥቅምት 27 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**:- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

**አመልካቾች**:- 1. አቶ ማሙሽ ወልደስላሴ

2. ወ/ሮ አፀደ ወልደስላሴ

ጠበቃ ውብሸት ሥነ ጊዮርጊስ

**ተጠሪዎች**:- 1. ወ/ሮ ሰብለ ወንድይራድ - ቀረቡ

2. ወ/ሮ የሺ ሙላት - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች ባቀረቡት አቤቱታ ወ/ሮ ውዴ ወልደስላሴ ባደረባቸው ሕመም ምክንያት ነሐሴ 21 ቀን 1989 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፤ ሟች በሕይወት እያሉ ነሐሴ 9 ቀን 1989 ዓ.ም እማኞች ባሉበት ባደረጉት ኑዛዜ በድሬዳዋ ከተማ ከፍተኛ 1 ቀበሌ 06 በአሁኑ አጠራር በቀበሌ 04 የሚገኘውን የቤት ቁጥር 839 ለእኛ ለአመልካቾች አውርሰውናል፤ ሁለተኛ አመልካችም አካለመጠን ላልደረሰችው ተማሪ ኮከብ እሱባለው ሞግዚት አድርገው ሾመውኛል፤ ስለዚህ በምናቀርበው ማስረጃ ተረጋግጦ የወራሽነት ማረጋገጫና አካለመጠን ላልደረሰችው ተማሪ ኮከብ እሱባለው የሞግዚትነት ማስረጃ ይሰጠን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የአመልካቾችን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ተቃዋሚ ካለ እንዲቀርብ ትእዛዝ በሰጠው መሰረት የአሁን አመልካቾች በተቃዋሚነት ቀርበው ቀደም ሲል አመልካቾች ተመሳሳይ አቤቱታ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርበው ጥያቄያቸው ውድቅ የተደረገ ሲሆን በይግባኝም ጸንቷል፡፡ ስለሆነም አመልካቾች ውሳኔ የተሰጠበትን ጉዳይ በድጋሜ ያቀረቡ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ውድቅ ሊያደርገው ይገባል በማለት የተከራከሩ ሲሆን በአማራጭም ሟች ውዴ ወ/ስላሴ አድረገውታል የተባለው ኑዛዜ በእድሜም ሆነ በጤንነት ረገድ እራሳቸውን በማያውቁበት ጊዜ የአሁን አመልካቾች እራሳቸው ፈጥረው ያዘጋጁትና በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተደረገ ከመሆኑም በላይ አመልካቾች የወ/ሮ ውዴ ልጅነትም ሆነ የሩቅ ዝምድና ስለሌላቸው የኑዛዜ ወራሽነት ጥያቄው ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለት የድሬዳዋ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ አቤቱታው አስቀድሞ በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ውሳኔ አግኝቷል የተባለውን በተመለከተ ፍ/ቤቱ አቤቱታውን ሳይቀበለው የቀረው አንድ ኑዛዜ ከተደረገ በኋላ በዚሁ ኑዛዜ መሰረት ወራሾች የንብረት ክፍፍል ከሚያደርጉ በስተቀር ኑዛዜ በፍ/ቤት እንዲጸድቅ ሕግ ስለማያስገድድ ኑዛዜ ይጽደቅልን በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሳኔ

ከመስጠቱ በስተቀር የኑዛዜ ወራሾች ናችሁ ወይንም አይደላችሁም የሚል የመጨረሻ ውሳኔ ስላልሰጠ ጉዳዩ አስቀድሞ እልባት አግኝቷል ተብሎ የቀረበው ክርክር አግባብነት የለውም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የኑዛዜውን ሕጋዊነት አስመልክቶ የተነሳውን ክርክር በተመለከተም ሟች በጤነኛ አእምሮና በነጻ ፈቃዳቸው ኑዛዜውን ስለማድረጋቸው በአመልካቾች ምስክሮች የተረጋገጠ ስለሆነና ሟችም ንብረታቸውን ለፈለጉት ሰው በኑዛዜ የማስተላለፍ መብት ስላላቸው ተጠሪዎች የአመልካቾችን የኑዛዜ ወራሽነት በመቃወም ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም ካለ በኋላ በሌላ በኩልም ሟች ኑዛዜ ያደረጉበት ቤት ባለሐብትነቱ በከፊል የእራሳቸው በከፊል ደግሞ የሟች ባቤታቸው የነበረ ስለሆነ ከእራሳቸው ድርሻ አልፎ የሟች ባቤታቸውንም ድርሻ ጨምሮ ያደረጉት ኑዛዜ ሕገ ወጥ ስለሆነ በድርሻቸው ልክ የተደረገው ኑዛዜ ብቻ ትክክል ነው ብሎ በዚሁ ልክ አመልካቾች ወራሾች ናቸው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታ ለድሬዳዋ ከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ለሰበር ቀርቦ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻው ነጥብ የተጠሪዎች የኑዛዜ ወራሽነት በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠው አግባብነት ባለው ሁኔታ ነው ወይንስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

ከዚህም አኳያ ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪዎች የኑዛዜ ወራሽነታቸው ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው አቤቱታቸውን ለድሬዳዋ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው የቀረበለትም ይሄው ፍ/ቤት በቅድሚያ የአመልካቾችን/የአሁን ተጠሪዎችን/ ምስክር ከሰማ በኋላ ተቃዋሚ ካለ ይቅረብ በማለት የጋዜጣ ጥሪ አድርጓል፡፡ እዚህ ላይ ተቃዋሚ ቢኖር ይቅረብ ተብሎ የተሰጠው ትእዛዝ አግባብነት ነበረውን የሚለው ነጥብ እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን ተቃዋሚ እንዲቀርብ ትእዛዝ መስጠት የነበረበት አመልካቾች አቤቱታቸውን እንዳቀረቡ ማስረጃ ከመስማቱ በፊት መሆን ይገባው ነበር፡፡ ተቃዋሚ የሚጠራበት አላማ የቀረበውን አቤቱታ ከማስረጃውና በአጠቃላይም ከሚቀርበው ክርክር አኳያ የበኩሉን ማስረጃና ክርክር እንዲያቀርብ እድል ለመስጠት ነው፡፡ ነገር ግን በተያዘው ጉዳይ ምስክሮች ከተሰሙ በኋላ ተቃዋሚ እንዲቀርብ ትእዛዝ መስጠቱ ተቃዋሚው በምስክሮች አመሰካከር ላይ የሚያነሳውን ክርክር/The right to confront witnesses/ የሚያጠብና ጉልህ የሆነ የሥነ- ሥርአት ጉድለት መፈጸሙን የሚያመለክት ነው፡፡

ስለሆነም የድሬዳዋ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካቾችን /የአሁን ተጠሪዎችን/ ምስክሮች ከሰማ በኋላ ተቃዋሚዎችን መጥራቱ እንደዚሁም ይ/ሰሚው ፍ/ቤት ይህንኑ ጉድለት ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የድሬዳዋ ከተማ ነክ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00409/99 በሰኔ 15 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመ/ቁ. 0134/99 ኀዳር 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሽረነዋል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የድሬዳዋ ከተማ ነክ ፍ/ቤት የተጠሪ ምስክሮችን በድጋሜ በመጥራት ግራ ቀኙ ባሉበት በመስማት ክርክሩን በድጋሜ ተመልክቶ እንዲወስን ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ